የካቲት ፲፯ ቀን ፳ ዓ.ም

# አዲዎስ! ሠላማዊ ትግል! ቻው ቻው

ከአያልነሽ

የሠላማዊ ትግሉ አልቀለታል፣ የሚያዋጣው የትጥቅ ትግልን ጨምሮ "ሁለ ገብ" ትግል ነው። ይህ ትግል ደግሞ በህቡዓዊ ትግል መደገፍ አለበት፣ ከሠላማዊ ትግል ጋርም ሳንታረቅ ተፋተናል። አንደርጋቸው ጽጌ (ከቀስተ ዳመና)

እኛ የምንታገለው ቅንጅት የጀመረውን "መንፈሳዊ የሠላማዊ ዴሞክራሲዊ ትግል" ከዳር ለማድረስ ነው። ይህንን "መንፈሳዊና ፍቅራዊ" ሠላማዊ ትግል ለማጧጧፍ አሁንም በተጠንቀቅ ላይ ነን። ሠላማዊ ትግሉን ለማስቀጠል በኢህአዴግ "ሕገ መንግሥት" ሥር ተሠልፈናል፣ ላንፋታም ተጋብተናል። ብርቱካን ሚደቅሳ (ከቀስተ ደመና)

የሠላማዊ ትግሉ ቀድሞም ቢሆን አልተጀመረም፣ ባልተጀመረ "ሠላማዊ ትግል" የ "ሠላማዊ ትግሉ አላዋጣም" ብሎ ሠላማዊ ትግሉን ማደናቀፍ፣ የጋንዲን መሥዋዕትነት ከንቱ ማስቀረትና ሻማ ሆኖ ዓርአያ የሆነንን ታላቅ ሰው፣ ደጋግሞ እንደመግደል ይቆጠራል። "ሠላማዊ ትግሉ" ገና አልተጀመረም፣ ለመጀመር ግን ውል ቋጥረናልና "አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ" የሚያወርደውን ማዘዣ ትጠባበቁ ዘንድ ትግስታችሁንና ትብብራችሁን እንለምናልን።
አዛውንቱ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም (የቀድሞው የቀስተ ደመና) መሥራች

የተጀመረው "የነጻነት ጎህ" እንዳይጨናገፍ አሁንም ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ይህ ቁርጠኝነት የሚገኘው ደግሞ "በሠለጠኑ ሰዎችና በሠለጠኑ ፖለቲካ አራማጆች" እጅ እንጅ፣ በአረጀና በአፈጀ የፊውዳልና "የጭቃ ሹም አምባ ገነኖች" በሚመሩትና በ"አክራሪ የ40 ዓመት" አሉባልተኞች በሚነዛ የ "ወሬ" ትግል አይደለም። "ሠላማዊ" ሆነ "የትጥቅ ትግል" ወይም "ሁለ ገብ" ትግልንና "ህዝባዊ እምቢተኝነት/አመፁን ለማቀጣጠልና የተጀመረውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማጧጧፍ፣ ተራራ ላይ ወጥቶ እያጠናሁ ነውና ፣ጥናቴን ጨርሼ ለኢትዮጵያ ህዝብ እስካወርድ ድረስ ሁሉም በተጠንቅቅ ሊጠብቅ ይገባዋል። ይህንን እልህ አስጨራሽ ትግል ማንም በጭፍንና ያለችሎታ ሊጀምረው አይገባውምና እባካችሁ! ታገሱን፣ታገሱኝ። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ (ከቀስተ ደመና)

በአደረግነው የሠላማዊ ትግል ተጋድሎ "ወያኔን ወደ መጣበት" ሳንመልስ ትግላችንን አናቆምም፣ የቀስተ ዳመና መሪዎች የሥልጣን ጥመኞችና ትግሉን አቀዝቃዥ ናቸው። የቅንጅት መሪ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸው። አቶ በድሩ አደም (ከቀስተ ደመና)

እኔ በዚህ አስደናቂ በሆነው ሠላማዊና "ሥር ነቀል" የትግል ተጋድሎ የተማረኩት ከረጅም ጊዜ በኋላ ራሴን "ከትግል" አግልዬ ከተቀመጥኩበት፣ ፕሮፌሰር መሥፍን ወ/ማሪያም ድንገት መንገድ ላይ ተገናኝተን፣ አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ምሳ ጋብዘውኝ ካጫወቱኝ በኋላ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን "የጀመረነውን የሠላማዊ ትግል ተቀላቅለህ ትግሉን አንድ እርምጃ ማስኬድ አለብህ ብለው" ስለጋበዙኝ ቀስተ ደመናን ተቀላቀልኩ። በቀስተ ዳመና መሪነትም "ኢሕአዴግ"ን ድባቅ መታነው። ከብርቱካን ሚደቅሳ አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት! ሞት ለኢንጃነር ኃይሉ! አርቲስት ደበበ እሸቱ (ከቀስተ ዳመና)

ይህንን "መንፈስና ፍቅር" ያሰረጽንበትን የሠላም ትግል በተጀመረው መንገድ "ዴሞክራሲን" እስክናሰፍን ድረስ መቀጠል አለብን፣ በኛ በኩል ይህንን የ "ሠላምና የዴሞክራሲ" ትግል 2 ዓመት ታስረን በመስዋዕትነታችን አቅጣጫ አመላክተናል። በጀመርነዉም መንገድ "ሕገ መንግሥታችንን" አክብረን በ"ሕገ መንግሥቱ"ሥር ሆነን ሠላማዊ ትግሉን እንካሄዳለን። እስከዚያው ግን በኔ በኩል ለጊዜው "አንድ የግብረ ሠናይ" ድርጅት አቋቁሜ በዚሁ ሥራ ለመሥራት ወስኛለሁ። ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም (ከቀስተ ደመና መስራች አንዱ)

ወይ ጉድ! ዝብርቅርቅ የቀስተ ደመና ፍሬ ከናፍሮች

የቀስተ ደመና የቁርጥ ልጅ የሆኑት አንዳርጋቸው ጽጌ ደግሞ ሰሞኑን "እንድትወያዩ" ጽሁፍ አቀርቤአለሁ በማለት ንብረትነቱ የሳቸው ነው ተብሎ በሚነገርለት ፓል ቶክ ላይ ቀርበው፣ አዲዖስ ሠላማዊ ትግል በማለት የትጥቅ ጥግል ጥሪ አሰምተዋል። ብዙ ጊዜ እኔ፣ እኔ ማለትን የሚያዘወተሩት አንዳርጋቸው ጽጌ፣  ዛሬም ይህንን "የትጥቅ ትግል" ስልት ቀድሜ ያቀረብኩት እኔ ነኝ በማለት "የሠላማዊ ትግሉ" እንዳበቃለት ስለታየኝና ይህንን እይታዬን ደግሞ ለማካፈል "አዲስ ግኝት" ይዤ ቀርቤአለሁና "ተወያዩበት" ብለው ወረቀቶቻችውን በአንዳንድ ድረ ገጾችም ላይ ለጥፈውልናል። የአንዳርጋቸው ልብ ከምር የማይቀበለውንና የማያምኑበትን፣ ነገር ግን የለበጣ "ሁለገብ" የትግል ስልትን መጠቀም አለብን የሚሉት "የዘወትር ሃሳብ አፍላቂ ነኝ ባዩ" አንዳርጋቸው ጽጌ ፣ ወያኔ የሠላሙን ትግል ከቁብ አልመቁጠሩን አውስተው እንዲያውም ይህንን "የሠላማዊ ትግል" አካሄዳችንን ከፍርኃት ቆጥሮታል በማለት ትግሉ "ሁለቱንም የትግል ስልት" ማካተትና መጠቀምን የግድ ብሏል ብለዋል። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በፖለቲካ ዕይታቸው ተመሳሳይነት የተወዳጁትንና በአምቻ ጋብቻ ያጠናከሩትን ወያኔ፣ "ጠላት" አይደለም ብለው የሚከራከሩት አንዳርጋቸው ጽጌ ይህንን እምነታቸውን ይበልጥ አጽንዖት በመስጠት በቅርቡ በኢ.ቴ.ኤን. ላይ ቀርበው አጠንክረው ገልጠዋል ወያኔ ጠላት አይደለም በማለት። እንደ ወያኔ "ግምገማ፣ ግምገማ" ማለትን የሚወዱትና በ"ግምገማ" ስም ቅንጅትን ገመገምኩ ብለው የቅንጅትን ውስጣዊ ሰውነት አጋልጠው በመስጠት ለወያኔ ሲሳይ እንዲሆን ያደረጉት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ይህንን ብዙ ሰው ለእሥርና ለእንግልት እንዲዳረግ የተደረገበትን "ግምገማዊ" የማጋለጥ ዘዴአቸውን፣ "ሥልጡን፣ ዘመናዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት" የሚል ማደናገሪያ ሽፋን አላብሰውታል። በዚሁ "ሥልጡን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት" በሚል "ግምገማዊ የማጋለጥ" አካሄዳቸውም ድርጅቱን ተቀላቀልኩ ባሉ በአራተኛው ወራቸው መስከረም 1998 ዓ.ም "<u>ቅንጅት እና የግንቦት 7ቱ ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች</u>" በሚል ባለ 19 ገጽ "የግምገማ"ወረቀት ጽፈው ድርጅቱን ለወያኔ በረከት አቀርበዋል። ይህ የ"ግምገማ" ወረቀት ከግንቦቱ 97 ምርጫ  በኋላ የተጻፈ ሲሆን ምርጫው በተካሄደ 4ኛው ወር ውስጥ መስከረም ላይ የተጻፈ ነበር። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ይህንን የግምገማ ጽሁፍ ጻፍኩ ካሉ በኋላ በቅንጅት ላይ የደረሰው አደጋና ከቃሊቲ እስር ቤት "ተፈርሞ" ወጣ እየተባለ በመጣ ወረቀት የቀስተ ደመና "ሊሂቆች" በውጭ ያለውን የቅንጅት ደጋፊን ሁሉ "በትግል ስም" አሽመድምደውታል። ይህ ጉዳይ እርግጥ ለጊዜው

ወያኔን ፋታ የሰጠው ቢመስልም ዛሬ ወያኔ ቅንጅት ከ5 ተከፈለ፣ ከ6 ተሰነጠቀ በማለት አሰረጎ ያስገባቸውን የጥቂት ግልሰቦችን ስብሰብ እንዳሻው እየበታተነና ሲፈልግም እየገጣጠመ በማዳነቀ፣ ሕጋዊነትም እሰጣለሁ በማለት ለትግል የተነሣሣውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያስተኛ ይፍጨረጨራል። ነገር ግን ይህ የህዝብ ትግል በዋለ በአደረ ቁጥር እየጠራና በአገር ቤትም ወያኔ በሕዝብ ላይ የሚያደርገውና የሚያደርሰው በደል ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ስለሆነ፣ ይህ የሕዝብ ትግል ግለቱ እየጨመረና እየጠዘ፣ ማን ምን እንደሆነና ማንነቱ እየተጋለጠ መሄዱን ደግሞ ወያኔም ሊደብቀው አልቻለም። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ ሶስት የ"ግምገማ" ጽሁፍ ያወጡ ሲሆን (ከዚያም በላይ ጽፈው ሊሆን ይችላል ) 3ቱን እንደሚከተለው አስፍሬዋለሁ።

- ያለፈውንና ያለንበትን አይቶ የወደፊቱን አቅዶ መንቀሳቀስ፥ አጭር መግቢያ፥ (27 ገጽ፣) ጠር 2000 ዓ.ም
- ለወደፊቱ ትግል ማመላከቻ የምርጫ 97 አጭር ግምገማ መንደርደሪያ (23 ገጽ) "ቀጣዩ ትግል ምን ይመስላል ?" የካቲት 20 /2000 ዓ.ም እና
- ከላይ መጀመሪይ ላይ ያስፈርኩት፣"ቅንጅትና የግንቦት 7 ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች" መስከረም 1998 ዓ.ም የሚለው ነበር። (19 ገጽ )

አቶ አንዳርጋቸው በግንቦቱ ምርጫ ወቅት ሲኖሩበት ከነበረው ከሎንዶን ተንደርድረው ወደ አዲስ አበባ ሲበሩ ወዳጃቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቀሰተ ዳመና አባልና ከዚያ ጋር ተከትሎም የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ (በሌሉበት እንዳስመረጡአቸው) በኢ.ቲ.ኤን ቴሌብዥን ላይ ተጠይቀው ሲመልሱ ተደምጠዋል። ሆኖም የቅንጅት ምክር ቤት አባል ነኝ ሲሉ የቀዩት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የቅንጅት ምክር ቤት አባል እንዳልነበሩና እንደያውም ወደ ቅንጅት እንድገባ አደረጉኝ/ጠየቁኝ ያሏቸው ግለሰብ ተጠይቀው "በፍጹም እኔ አላስገባሁትም" በማለት መመለሳቸው አይዘነጋም። በውጭ(በዲያስፖራው) ያለውን ትግል እንድመራ"ሕጋዊ ፈቃድ" አግኝቻለሁ በማለት በቅንጅት ስም ሲያከናውኑት ለቀዩት ተግባር ሁሉ ከሀገር ቤት ከቃሊቲ እሥር ቤት በሚላክልኝ ደብዳቤ መሰረት "የፕሬዚዳንታችን" ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ፊርማ የተቀመጠበት ወረቀት በሰጠኝ ፈቃድ ነው ሥሰራ የቀየሁትም በማለት በኵራት ሲገልጹ ቀይተዋል። የተከበሩ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ከእስር ተፈትተው ወደ አሜሪካ መምጣታቸው ሲረጋገጥ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ጋር መገናኘቱን እንዳልፈለጉና እንዲያውም ወደ አሜሪካ ለመግባት ቀናቶች ሲቀሩ፣ "ከመሪዬ" ባገኘሁት "ሕጋዊ ፈቃድ ነው" የቅንጅት "ቻፕተሮችን" ሳዋቅር የቀየሁት ሲሉ የሠነበቱት እኝህ ሰው በዚያው አፋቸው መልሰው ክቡር

ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን "አምባገነን" መሪ ናቸው በማለት አጣጥለዋቸዋል። አንዳርጋቸው አሁንም "ቀጣዩ ትግል ምን ይመስላል" ብዬ አወጣሁ ያሉትን ባለ 23 ገጽ ጽሁፋቸውን "ራሳቸው ያፈለቁት ሃሳብ" አስመስለው 'ሁለ ገብ' ትግል ሲሉ፣ በሕጋዊነት ለመንቀሳቀስ ያልተፈቀደላቸው ኃይሎች ደግሞ ቀደም ብለው "ሁለ ገብ" ትግሉን መርኃቸው አድርገው በህቡዕና በሚያመቻቸው መንገድ የሚታገሉ ባንድ በኩል እንዲሁም በ"ትጥቅ ትግል" ብቻ ነው ወያኔ የሚወድቀው ብለው ወያኔን ለመጣል የሚታገሉ ኃይሎች ደግሞ በሌላ በኩል መኖራቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀውና ወያኔም ሊሸሽገው የማይችለው ሐቅ ነው። የቅንጅት መመሪያ የሆነውን "ማንፌስቶ" የጻፍኩለት እኔ ነኝ ባዩ አንድርጋቸው ፅጌ

> "የሠላሙ ትግል አብቅቶለታል፣ አሁን ያለው አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው፣ ይኸውም በህቡዑ ትግል የተደገፈ ትጥቅ ትግልና ሁለገብ ትግል ነው መፍተሔው"

በማለት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በቅርቡ ጻፍኩ ያሉትን እጅ እግሩ የማይጨበጥ፣ በጨለምተኝነት ላይ የተመሰረተና የተደመደመ "እኛ ያልተቆጣጠርነው" ትግል መንቀሳቀስ የለብትም በሚል ዓይነት መልዕክታቸውን የሰነዘሩበትን ጽሁፍ (ስለ ዴሞክራሲያዊ ትግሉ አንዳንድ ኃሳቦች የ ዶ/ር ብርሃኑን ጽሑፍ ይመልከቱ) ነው ዛሬ አንዳርጋቸው ጽጌ በፓልቶክና በጽሁፋቸው የደገሙት። "ማንም ምንም ቢል" ጉዳዬ አይደለም የሚሉት አንዳርጋቸው ጽጌ በሰርጥ እየገቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አንድ እርምጃ ከፍ ሲል ለማቀዝቀዝ፣ ወያኔ ፍትኃዊ ያልሆነውን አገዛዙንና ኢትዮጵያን ወደ እንጦሮጦስ የሚያወርዳትን አካሄዱን እንዲቀጥል እድሜና ጊዜ እንዲያገኝ የሚያበረታታውን አካሄዳቸውን ትክክለና ፍጹም እንከን የማይወጣለት "አማራጭ" አድረገውም ያቀርቡታል። አቶ አንዳርጋቸውን ከሌሎች የቀሰተ ደመና አጋሮቻቸው ለየት የሚያደርጋቸው ደግሞ፣ ወዳጃቸው የሆነውን ወያኔ/ኢህአዴግን ወያኔ፣ ወያኔ እያሉ ሲጠሩ በአክራ (ጋና) ቀይታቸው ወቀት የተገናኙት መለስ ዜናዊ ሙሉ ፈቃዱን የሰጣቸው አስመስሏቸዋል። ሁሌም የሁሉም ነገር ጀማሪና አቅጣጫ አመላካች እኔ ነኝ የሚሉት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌና ቡድናቸው፣ በምንኖርበት አገር በዓይናችንና በጆሮችን ላይ ተኝተው የክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን ፎቶ ግራፍ በመለጠፍ ቡድናቸውና እሳቸው ስብሰባ ሲጠሩና በሳቸው ስምም ብዙ ገንዘብ በመሰብሰብ (ከ1.000.000 ብር በላይ) ገቢ ማድረጋቸውን በአደባባይ ተገልጧል። "የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ልጅ ይጥፉ" የሚለው ስለ እውነት ህያውነት የሚገለጽበት "የፋራው" የአነጋገር ይትብኃላችን የማይገዛቸውና የማይቀብሉት "ሥልጡኑ" አንዳርጋቸው ጽጌ እንዲያውም ይህ ይትባሃል ኋላ ቀርና "100 ዓመት" ካስቆጠርችው ኢትዮጵያ ጋር ያልተዛመደና የማይሄድ ነው በማለት ያጣጥሉታል። ይህ ከ1.000.000 ብር በላይ ከሕዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ሲገደልና

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የቆሙ የአንድነት ኃይል ድርጅቶችን ከሥር ሥር እየተከለ ጠልፎ ለመጣል ቡድናቸው እየተጠቀመበትና እያዋለው መሆኑን በገሃድ እየተመለከትን ነው። አሁንም ያሰሙት ''የትግል ስልት ጥሪ'' ሌላው ተጨማሪ አብነት ነው። ለዚህም ነው በተመሳሳይ መንገድ የቀሰተ ደመና መሥራች የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ኦክቶበር 2007 (አውሮ. አቆጣ.) በጀርመን ድምጽ ራዲዮ ላይ ''ኃይሉ መምራት አልቻለምና ልጄ ብርቱካን ሚደቅሳ መሪነቱን ተረክባ ቅንጅትን ታድን'' ያሉትን ዘንግተው አሁን ላቋቋሙት አዲስ ድርጅት ''አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ'' መሪ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸውና ወንበሩ ክፍት ሆኖ ይጠብቃቸዋል የሚል ቡታ የሚያስነግሩት። አንዳርጋቸውም በሰሞኑ ንግግራቸው ከቅንጅት ተሰናብቻለሁ ብለው፣ የማደርገው ነገር ሁሉ ግን ''በግሌ'' ነው በማለት፣ ወዳጅ ላሉት ወያኔ የአንድነት ኃይሉን ግስጋሴ አስቀድሞ ለመቅጨት ይረዳው ዘንድ ''የመወያያ ጽሁፍ'' አውጥቻለሁና ''ተወያዩበት'' የሚሉን። ይህ ሁሉ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ''በጠላትነት'' የሚያዩአቸውን ኢሕአፓንና በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ሥር የሚመራውን ቅንጅትን በወዳጃቸው ወያኔ/ኢህአዴግ ለማስፈተሽ ነው። በስመ ''ግምገማና'' ''እንድትወያዩበት'' ነው በሚል መሰመሩን የሳተና በአምባገነንነቱ ዓለም ያወቀውን ወያኔን እንዲጠነቀቅና፣ አስቀድሞ እንዲዘጋጅ የሚያመቻች ግብዣ ነው። በተጨማሪም አንድነት ኃይሉ የእንቅስቃሴውን አቅጣጫ በአደባባይ እንዲያወጣና በሰመ ''ዴሞክራሲያዊነትና ግልጽነት'' ስም ምስጢራዊ አሰራራቸውን ለመፈተን ጭምር ነው። ወደድንም ጠላንም በወያኔ ሥር በወደቀችና በምትገዛው ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በወያኔ በታሰረበት ሁኔታ፣ እንዲህ ዓይነት አሳሳችና ''ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ አወያይና ውይይትን ጋባዥ ወረቀት፣ ግምገማና ወዘተ ...'' የሚሉ አዘናጊ ጽንሰ ሐሳብን ማቀንቀን፣ ኢትዮጵያን የሚጎዳና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት የሆነውን ወያኔን የሚጠቀም ነው። ስለዚህ ጎበዝ አሁንም ለድጋሚ እንዳንታለል፤ ጠንቀቅ እንበል ብሎ ማስታወስ ያስወቅስ ይሆን? ከሆነም ለወቀሳው ዝግጁ ነኝ። ግምገማ! ግምገማ! ግምገማ! ምን ዓይነት ግምገማ? ተከታዩን በሚቀጥለው።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!

ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን

ማርች 23/ 2008